# አማርኛ ጥንታዊውና ታሪካዊዉ የኢትዮጵያ ቋዋንቋዋ

አማርኛ ኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም ከተሞችና ባብዛኛው የገጠር ክፍል ሀገራት የመግባቢያና ብሄራዊ ቋዋንቋዋ ነው፡፡ ባለንበት ዘመን አማርኛ በጂቡቲ ሱዳንና ኤርትራ ዉስጥም ብዙ ተናጋሪዎች ያሉት ሲሆን ከዚያም አልፎ በመካከለኛው ምስራቅ በኤሮጳ በሰሜናንና ደቡብ አሜሪካ ጭምር ተናጋሪዎቹ ከጊዜ ወድ ጊዜ እየጨመሩ መምጣታቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ይህ ቋዋንቋዋ በዓለም ውስጥ በስፋት ከሚነገሩ የሴማዊ ቋዋንቋዋዎች አረብኛን ተከትሎ ሁለተኛው ሲሆን በስፋት የሚነገረዉ መፍለቂያው ከሆነውና ከፍተኛዉን የህዝብ ብዛት ከሚይዘው ከአማራ አካባቢ ነው፡፡ በአሁኑ ሰአት በመላው አለም ከ80 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ይህንን ቋዋንቋዋ እንድሚናገር ይገመታል፡፡ በግእዝ "አም" ማለት "ህዝብ" ሲሆን "ሃራ" ማለት ደሞ ነጻ ማለት ነው፡፡

ስለዚህ "አምሃራ" ማለት ነጻ ህዝብ ማለት ነው፡፡ ይህ መጠሪያ ኢትዮጵያዊ ዜግነትን ያጎናጸፈው ኢትዮጵያ እንደ ህጋዊ መንግስት ከተመሰርተቹበት (ከክርስቶስ ልደትበፊት ፲፱ ዓመት) በሰሎሞን ስረወ መንግስት ዘመን በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ ነው፡፡ በራሱ በአማርኛ ቋዋንቋዋም የአማረ የተዋበ ወይም ደስ የሚል ቆንጆ ማለት ነው፡፡ ዛሬ ስሙ በጊዜ ብዛት ተዛብቶ አክሱም የሚባለው የስልጣኔና የግዛት ማእከል በዚያን ጊዜ "ያገር ሹም" በመባል እንደሚጠራ ተመራማሪወቹና ጥንታዊ ጽሁፎቹ አረጋግጠዋል፡፡ የስልጣኔ

| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ | ሰ | ሸ | ቀ | ቋ | በ | ተ | ቸ | ኀ | ኈ | ነ | ኘ | አ |
| h | l | ḥ | m | ś | r | s | š | q | qu | b | t | č | ḫ | ḫu | n | ñ | ʾ |
| [h] | [l] | [ħ] | [m] | [s] | [r] | [s] | [ʃ] | [kʼ] | [kʷ] | [b] | [t] | [ʧ] | [h] | [hʷ] | [n] | [ɲ] | [ʔ] |
| ከ | ኸ | ወ | ዐ | ዘ | ዠ | የ | ደ | ጀ | ገ | ጐ | ጠ | ጨ | ጰ | ጸ | ፀ | ፈ | ፐ |
| k | h | w | ʿ | z | ž | y | d | ǧ | g | gu | ṭ | č̣ | ṗ | ṣ | ẓ | f | p |
| [k] | [h] | [w] | [ʔ] | [z] | [ʒ] | [j] | [d] | [ʤ] | [g] | [gʷ] | [tʼ] | [ʧʼ] | [pʼ] | [ts] | [ts] | [f] | [p] |


ማእከሉ በጸረክርቲያኑዋ ዮዲት ጉዲትና በአካባቢው የእስልምና ሃይማኖት መስፋፋት የተነሳ ሲዳከም ቦታዉን ያስተዳድሩ የነበሩት አማሮቹ በ፱ኛው ዓም ሙሉ ሰራዊታቸዉን የአስተዳደር መዋቅራቸውን ቋዋንቋአቸዉን ባህላቸዉንና ሃይማኖታቸው ይዘው ወደ ደቡብ ማለትም ከዚያም በፊት ወደነበሩበት የአሁኑ የአማራ አካባቢ (መርሃቤቴ ላይ) ሰፈሩ፡፡ከዚያም ወዲህ በ፮፮ ዓም አማርኛ የዛጉየ ስርወ መንግስት ብሀራዊ ቋዋንቋም ነበር፡፡

አማርኛና ግእዝ ስለማይነጣጠሉና አንዱ በሌላው ዉስጥ ሰርጾ ስለሚገኝ ቀደምት አማሮቹ ግእዝን ለቤተክርቲያን (ለመንፈሳዊ) አገልግሎት ብቻ ሲያዉሉት አማርኛን ደግሞ ለአስተዳደር ለወታደራዊ ግንኙነትና ለመዝናኛ (ለዘፈንና ለመሳሰሉት) እስከዛሬ ጠብቀው ይጠቀሙበታል፡፡ የአማርኛን ፊደላት ኢትኤል የተባለው ካህን ዓለም በተፈጠረቹ ፲ኛው ትዉልድ በመለኮታዊ እርዳታ እንደቀረጻቸው ይነገራል፡፡ ይህም ማለት አማርኛና ግእዝ የመጀመሪያዎቹ የሰው ልጅ ሃሳቡን በጽሁፍ ያሰፈረባቸው ቋዋንቋዋዎቹ ናቸዉ ማለት ነው፡፡

አማርኛ ከግእዝ ሌላ ተጨማሪ ፊደሎች አሉት። እነዚህ ተጨማሪ ፊደሎች ማንኛዉንም በድምጽ የሚሰማ ነገር ሁሉ ለመጻፍ የሚያስችሉ ሲሆኑ አሁን ላለበት የእድገት ደረጃዉና ለተመራጭነቱ ከፍተኛዉን ድርሻ ይይዘሉ።

አማርኛ ከጊዜው ጋር ራሱ እያደገ መጣ እንጅ የሚጠቀሙበት ኢትዮጵያዉያን ምንም ያህል ጥረት አላደረጉም። ነገር ግን ታሪካዊ መሰረቱ ከግእዝ ጋር ረጅምና አንድ በመሆኑ ራሱም ሌሎችን የመማረክና የመወደድ ተሰትኦ ስላለው የሚታተሙት ጽሁፎችና የተናጋሪዎቹ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመሄድ ላይ ነው። ለዚህም እንደ ማስረጃ ልትጠቀስ የምትችለው አሜሪካን ሃገር ዉስጥ እዉቅናን ያገኘችዉ ትንሹዋ ኢትዮጵያ ጎዳና ናት።

እንደ ኤሮፓ አቆጣጠር ፪፻፷ አም ከፋለ ዓለሙ የተባሉ ተጒዋዥ ለእረፍት ወደ ሞሮኮ ሄደው ፌዝ የተባለዉን መዲና ሲጎበኙ በአንድ ታሪካዊና መንፈሳዊ ህንጻ መግቢያ ላይ በአማርኛ ፊደሎች ያጌጠ የስነ ጥበብ ስራ አግኝተዋል። ይህንን አስደናቂ የ፩፪ኛው ክፍለዘመን በአማርና ፊደሎች ያጌጠ የጥበብ ስራ በተንቀሳቃሽና በማይንቀሳቀስ ምስል ቀርጸው ለአለም ህዝብ አሳዉቀዋል።




እኛም ከዚህ ጽሁፍ ጋር አቅርበነዋል። ይህ የሚያመለክተው ምናልባት አማርኛ ከኢትዮጵያ ተነስቶ ሰሜን አፍሪካንንና መካከለኛውን ምስራቅ ሳያዳርስ እንዳልቀረ ነው። በተጨማሪም [1]አማርኛ ግእዝና ይብራይስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ በመሬት ላይ እንደሰው ሲኖር የሚያስተምርበትና ይነጋገርበት የነበረዉን አራማይክ የተባለዉን ቋውንቁዋ እንደሚጋሩ ተመራማሪዎች ይገልጻሉ።

---

[1] ከፍዓለሙ